December 19, 2022 11:27 AM AMHARIC

# ወቅታዊ ሕመምን መከላከል

**COVID፣ ጉንፋን፣** እና **RSV** ኢንፌክሽኖች እየተስፋፉ ነው። በወረርሽኙ ወቅት የምንወስዳቸው እርምጃዎች አሁንም ከእነዚህ ህመሞች ምርጡ መከላከያዎቻችን ናቸው።

## በየቀኑ በሽታን መከላከል






- ሲታመሙ ቤት ይቆዩ። የታመሙ ሰዎች አካባቢ ከመሆን ይቆጠቡ።
- ምልክቶችን ይመልከቱ፣ በተለይም ከታመመ ሰው ጋር አብረው ከነበሩ።
- ብዙ ጊዜ እጅዎን ይታጠቡ።
- እንደ የበር እጀታዎች፣ ስልኮች እና የቲቪ የርቀት መቆጣጠሪያዎች ያሉ በተደጋጋሚ የሚነኩ ቦታዎችን ያጽዱ።
- COVID-19 የበሽታ ምልክቶች ካሉብዎት ይመርመሩ።
- በየአመቱ የጉንፋን ክትባት እና COVID-19 ክትባቶችን እና ማበረታቻዎችን እንደሚመከረው ይውሰዱ።

## በመተንፈሻ አካላት ህመም ወቅት




ሌሎች ድርጊቶች ልጆችን በትምህርት ቤት እንዲቆዩ፣ ወደ ሥራ ወይም ስብሰባ እንዳይመጡ ለመከላከል እና የሆስፒታሉን ስራ ቀላል ለማድረግ ይረዳሉ፡-

- በቤት ውስጥ ወይም ሰው በተሰበሰበበት ቦታ የአፍ እና አፍንጫ መሸፈኛ ያድርጉ።
- ለከባድ በሽታ ተጋላጭ ከሆኑ ሰዎች ጋር መጎብኘትን ማዘግየት፣ ወይም በአካባቢያቸው በሚሆኑበት ጊዜ እንደ የአፍ እና አፍንጫ መሸፈኛእና አካላዊ ርቀት ያሉ ተጨማሪ መከላከያዎችን ይጨምሩ።
- አነስ ያሉ፣ ከቤት ውጪ ስብሰባዎችን ያካሂዱ።
- ለተሻሻለ የአየር ዝውውር መስኮቶችን እና በሮች ይክፈቱ።

| | COVID | FLU | RSV |
|---|---|---|---|
| በአየር ውስጥ በቀላሉ ይሰራጫል | √ | | |
| ከአንድ ሰው አፍንጫ ወይም አፍ በሚወጡ የንፋጭ ጠብታዎች ይተላለፋል | √ | √ | √ |
| በጠንካራ እና ለስላሳ ወለል ላይ መኖር ይችላሉ እና እነዚህን ቁሳቁስ በመንካት ህመሙን ሊያሰራጭ ይችላል | | √ | √ |
| ክትባት እዚህ ይገኛል | √ | √ | |
| **ለነፍሰ ጡር ሴቶች**፣ አረጋውያን፣ እና **በጣም ዝቅተኛ የበሽታ መከላከል አቅም ላላቸው** ሰዎች **ከፍተኛ አደጋ** ሊሆን ይችላል። | √ | √ | √ |
| **ለአራስ ሕፃናት እና ለህፃናት ከፍተኛ አደጋ ሊሆን ይችላል።** | | √ | √ |

## ለከባድ COVID-19፣ ጉንፋን፣ ወይም RSV ከፍተኛ ተጋላጭነት ካለዎት

ከአቅራቢዎ ጋር ግንኙነትዎን ይቀጥሉ። የሕክምና አገልግሎት ሰጪ ከሌልዎ፣ ርዳታ ለማግኘት ወደ **211** ይደውሉ። አቅራቢያዎ የአፍ እና አፍንጫ መሸፈኛ እንዲያደርጉ ወይም ሌሎች ቅድመ ጥንቃቄዎችን እንዲያደርጉ ሊመክርዎ ይችላል። ከታመሙ፣ ምርመራ ማድረግ ወይም መታከም እንዳለብዎት ለመወሰን ሊረዳዎት ይችላሉ።

**ከታመሙ ምን ማድረግ እንዳለብዎ ሌላኛውን ጎን ይመልከቱ።**

## ከታመሙ

አብዛኛዎቹ ሰዎች ከእነዚህ የመተንፈሻ አካላት በሽታዎች በራሳቸው ያገግማሉ። ቤት ይቆዩ እና ጥሩ ስሜት እንዲሰማዎት አብዛኛውን ጊዜ የሚያደርጉትን ያድርጉ፡- መተኛት፣ እረፍት ማድረግ እና ብዙ ፈሳሽ መጠጣት።

## እርስዎ ወይም ልጅዎ እነዚህ ከባድ ምልክቶች ካጋጠሟችሁ 911 ይደውሉ፡-

- ለመተንፈስ መቸገር
- በደረት ወይም በሆድ ላይ ሕመም ወይም ግፊት መሰማት
- ፈሳሽ ነገር መጠጣት አለመቻል ወይም ከጠጡ በኋላ ማስመለስ
- ያልነበረ ግራ መጋባት ወይም መንቃት አለመቻል
- ሰማያዊ መሰል ወይም ግራጫማ የመሰለ ከንፈር ወይም ፊት



## ከታመሙ ነገር ግን ከሌሎች ጋር መሆን ካለብዎት

- በአፍንጫዎ እና በአፍዎ ላይ በደንብ የሚገጥም የአፍ እና አፍንጫ መሸፈኛ ያድርጉ።
- በተለይም አፍንጫዎን ከተናፈጡ በኋላ እጅዎን ብዙ ጊዜ ይታጠቡ።
- ሳልዎን በቲሹ ወይም በእጅጌዎ ይሸፍኑ።
- ከተቻለ ከሌሎች ጋር የተወሰነ ርቀት ይኑርዎት።
- የክፍል አየር ዝውውርን በሌሎች ዙሪያ ያሻሽሉ፣ ለምሳሌ መስኮት በመክፈት።

## ከሌሎች ጋር መሆን የሚችሉት መቼ ነው?

ሰዎች በአጠቃላይ ወደ ሥራ፣ ትምህርት ቤት እና ሌሎች እንቅስቃሴዎች በሚከተለው ጊዜ ሊመለሱ ይችላሉ፡-

- ትኩሳትን የሚቀንሱ መድኃኒቶችን ሳይጠቀሙ ቢያንስ ለ 24 ሰአታት ትኩሳት ካላሳዩ፣ **እና**
- ምልክቶቹ በእርግጠኝነት ከተሻሻሉ፣ **እና**
- በደንብ እየበሉና እየጠጡ ከሆነ፣ **እና**
- የአፍንጫ ንፍጥ እና ሳል መለስተኛ ሆነው በእንቅስቃሴዎች ውስጥ መሳተፍ እና እጃቻቹህን ንፁህ ለማድረግ ከቻሉ።

**ንፍጥዎ እና ሳልዎ እስኪጠፉ ድረስ በሌሎች ዙሪያ የአፍ እና አፍንጫ መሸፈኛ ማድረጎትን ይቀጥሉ።**